# በኢትዮጵያ አለ፡ ብሩሕ ተሰፋ!

ከብዙ ዓመታት መጠፋፋት በኋላ ከአንድ ዘመዴ በሰው ፡ሰው በዘመኑ መገናኛ ብዙሃን ፓል ቶክ በሚባለው ተገናኘን። ሰለዘመድ አዝማድ ከተጠያየቅን በኋላ ከተለመደው የሃገር ጉዳይ ገባን። ዘመዴ በኤርትራና በኢትዮጵያ ያሉትን ሁኔታዎች ጠንቅቆ የሚያውቅ ነው። ስለሆነም ግምገማውን ቀጠለ። 'መለሰ ዜናዊ የኢሰያስ አፈወርቂ የአንድ ሣንቲም ሌላው ገጽታው ነው' በማለት አስቀመጠው። ሻዕቢያ በመካከለኛ ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙትንና የሚቃወሙትን ወደ ሳዋ እስር ቤት ሲሽኛቸው ወጣቱን ግን በራሱ ቀርፆታል። የኤርትራ ወጣት በንቃቱ በአስተሳሰቡ በአለባበሱ በአቀራረቡ ያልተደነቀውን ያህል ዛሬ አጉልፋቶ ሆኗል። የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግንባር ግን አልተሳካለትም።የሕዝብን ልብ አላገኘውም። በሕዝብ እውቅና ያለቸውን እንዲሰደዱ ቢያደርግም፤ ለሃገር ተሰፋ ያላቸውን ወጣቶች በሰውር ቢያስገድልም፤ ለሃያ ዓመት ጥላቻን ቢሰብክም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለወያኔ አልተበረከከም። ስለዚህ በኢትዮጵያ አለ ብሩሕ ተሰፋ' በማለት የታየውን አጫወተኝ።

በእርግጥ በኢትዮጵያ ብሩሕ ተስፋ አለ። የዋልጌ ጥርቅም የትግራይ ሕዝብ ነፃነት ግንባር በማለት በሃገራችን ላዕላዊነትና በሕዝባችን ላይ ያደረሰውን ጥፋት ወሰን የለውም። ገና በዕጭጩ በለጋነቱ ጀምሮ ያከናውን የነበረውን ዕኩይ ተግባሩን በውስጡ ኖረው የታዘቡትን አቶ ገብረ መድሕን አርአያ ግልጥልጥ አድርገው አሰምተውናል፤ በማስረጃ አስደግፈው አሳይተውናል።

ይህ የጥፋት መልክተኛ ቡድን ጎረቤታሞች እሣት እንዳይጫጫሩ፣ ቡና እንደይጣጡ በአጋምና ቀጋ አጥሮ፤ መስኮች በሚያበቅሉት አዝዕርት ብሳናና ክትክታ ወሰን ለይቶ፤ ክልል ፈጥሮ፤ በቋንቋና ጎሣ ሕዝብን ለያይቶ፤ እርስ በእርስ ለማጫረስ፣ የሩዋዳውን የዕልቂት ተመስሌ ኢትርሐሞይን ቢሰብክም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወይ ፍክች አለ።

የወያኔ ፖለቲካ ባዶውን ቀረ። እውነት መስሏቸው የተወናበዱም ወደ ሰላማዊ ኑሯቸው ተመለሱ። የተጉዳዱም ይቅርታ ተጠያየቁ።

አሁን ያለው ሁኔታ በሕብረተሰባችን ውስጥ የሚነገር ተረት አስተወሰኝ።

አንዲት ሴት ሥጋ ያምራትና ያለቻትን ድመት አርዳ ትበላለች። ይህን ምሥጢር ለጎረቤቷ ትነግራታለች። ይህ ድርጊት ሕብረተሰቡ ቢሰማ ይህቺን ሴት ያገላታል። ከጎረቤት እሣት አትጭርም፤ ወንዝ አብሯት የሚወርድ አይኖርም፤ ቢያማት ውኃ የሚያቀብላት አይታሰብም። ልክ 'ሃራም ፎን ከርከሮ' እንደሚባለው ነው። በሙስሊሙ ሕበረተሰባችን አንድ ሰው የከርከሮ ሥጋ በላ አይደለም፤ ነካ ከተባለ ፍጹም ይገለላል። የዛች ድመቷን አርዳ የበላች ሴት ጉዳይ የዛን ያህል የከፋ ነው። መቼም ሁሉም ነገር እንደነበር አይቀይምና መልካም ወደመጥፎ መጥፎም ወደ መልካም ይለወጣል። ያ ሆነና ድመቷን አርዳ የበላችው ሴትና ምሥጢረኛ ጎረቤቷ ይጣላሉ። ከደጃፋቸው ቀመው የስድቡን ወንጭፍ መወራወር ይጀምራሉ። ድመቷን አርዳ የበላቸው ከሕብረተሰቡ ውጪ የሚያደርጋትን ምስጢር ጓደኛዬ ታወጣለች በሚል ያንን ለማቻቻል አጥንት ሰባሪ፣ ጋብቻ ከልካይ የሆነውን ስድቧን እንደሮኬት ታስወጭፈው ጀመር። ያንን የሰሙ ጎረቤታሞች አበስኩ ገበርኩ አሉ ። ገብስ ገብሱን የተሳደበችውን ግን አከበሯት። እምነት የሚጣልባት ሴት ናት በማለት አደነቋት። በመጨረሻ ያቺ ድመቷን አርዳ የበላቸው ሴት ባደረገቸው ሁሉ ተጸጽታ ጓደኛዋንም ጎረቤቶቿንም በሃገር በሕል መሠረት ይቅርታ ጠይቃ ለሂሊናዋ እረፍት ለሕብረተሰቧ ሰላም ፈጠረች።

የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ አለት ደንጋይ የጠነከረ ባሕልና ወግ ያለው ሕዝብ ነው። በፓለቲካ አውሎ ንፍስ ወደ አየለው የሚነፍስ አይደለም። ማንነቱን ከማንም ተጽኖ ጠበቶ የኖረ ሕዝብ ነው። ደሃ መሆን የእኔነትን ኮራትና ክብር የሚያሳጣ አይደለም። ስለሆነም የኢትዮጵያ ሕዝብም ራሱን አዋርዱ ንዋይን የመረጠበት ጊዜ አልነበረም።

በወገን ላይ አጉል መኮፈስን ይቃወማል፤ አንዱ ከሌላው ዝቅ አድርጎ መመልከት ወይም አንዱን ከሌላው አብልጦ ማሞመኮሸት ሕብረተሰብን እንደነቀርሳ አመንምኖ የሚገድል ደዌ መሆኑን ይረዳል።

ለምሳሌ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የጀርመኑ አዶልፍ ሒትለር የአርያን ዘር ምርጥ ዘር ነው በማለት ሌላውን ዘር ለማጥፋት ተነሣ። ሰድስት ሚለዮን የሚሆኑ አይሁዳንን ገደለ። ጀርመን በዓለም ሕብረተሰብ ተወገዘች። ጀርመኖችም አፈሩበት። የሰው ልጅ ግንዱ አንድ ነው።ሒትለር የአርያን ዘር ምርጥ ዘር ነው ሲል ዋሸቷል። ይህም አነጋገሩ በዓለም አንደኛ ውሸታም አድርጎታል።

መለስ ዜናዊ የትግራይ ሕዝብ 'ወርቅ ነው' ሲል ዋሸቷል። የትግራይ ሕዝብ ከቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለማለያየት የተጠቀመው ስልት ነው። ፋሽሽቱ መሶሎኒ ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት ተጠቅሞበታል። የተጋፈጡትን ሁሉ 'አማራ' በማለት

የአንድ ሕብረተሰብ ክፍል ብቻ እንደተዋጋው አስመስሎ ሌሎችን ዋጋ አሳጥቶ በተዋጉት ላይ ኃይል ለማስባሰብ የተጠቀመበት ስሌት ነበር። የትግራይ ሕዝብ ነፃነት ግንባርም ያንን ስልት በመጠቀም ነበር 'አማራ' የሚለውን የሕብረተሰብ ክፍል መርጠ አውጥቶ፤ ለዘመናት በሃገሪቱ ውስጥ ለተፈጠሩት ዕኩይ ተግባራት በሙሉ ተጠያቂ አድርጎ ለማለያየት ተጠቅሞበታል። እየተጠቀመበት ይገኛል።

በትግራይ ሕዝብ ነፃነት ግንባር ስም ከምኒሊክ ቤተመንግሥት እየኖረ ሕዝብን በጠራራ ፀሐይ እየገደለ፤ የሃገርን ዕርስት ለባዕዳን እየሸጠ፤ ወሰን ቀርሶ ለባዕድ ሃገር እየሰጠ፤ ሃገሪቱን ወደብ አልባ አድርጓት ፤ ማንም ኢትዮጵያዊ የትግራይ ሕዝብ ይህን ፈጸመ አላለም።

'በኢትዮጵያ አለ ብሩሕ ተስፋ' ያልኩት የወያኔ የቅርብ አንጋቶቹ ሳየቀሩ የከፋፍለህ ግዛ ደባ እነርሱም እየተረዱት መምጣታቸው ነው።

የወያኔ ገዕባ ከመሬቱ እየተቃረበ መምጣቱን የሚጠረጠሩ ካሉ መልስ ዜናዊ የራሱን መወጫ እስከሚያዘጋጅ ድረስ በቀብጺ ተሰፋ እንዲቀዩ በጨት ሚርቃና ሌተ ተቀን ቱፍታውን የመቀበሉ አሚን ባዮች ሙናፊቆች ብቻ ናቸው። ይህም ሲባል ያለ መስዋዕትነት ደል ይመጣል ማለት አይደለም። እያንዳንዱ ዜጋ የሃገር ባለቤትነቱን ሃለፊነት የሚወጣበት ጊዜ ነው። እንደብልጬ ተሸሽጎ ሌላው በከፈለው አለሁ ማለቱ የተበላ ዕቁብ ነው። ልዩ ፡ ልዩ ክንስሣሮች እየፈጠርን ለፍረሃትና ለድቁርናችን ከለላ መስጠት ያከተመለት ብሩሕ ተሰፋ የታየበት ጊዜ ነው። በዘር ማጥፋት የተከሰሱት መለስ ዜናዊና ቡድናቸው እንኳን ሃገር ሊመሩ ሰላማዊ ሕዝብ ከሚኖርበት አካባቢ መወገድ ያለባቸው ነው። ሥፍራቸው እስር ቤት ነው። የጸጥታ ጠባቂው ኃይል፣ በሃገር ደህንነት ስም የተሰማሩ ዜጎች፣ የሃገሪቱ መከላከያ ኃይልን ጨምሮ፣ የዜግነት ግዴታን የመወጫው ጊዜው አሁን ነው። ሁላችንም እንደዜጋ ተከብረን ተፈርተን የምንኖረው ይህቺን ሃገራችንን ከአባቶቻችን እንደተረከብናት ለልጅ ልጆቻችን ስናስተላልፋት ብቻ ነው።

አሁን በሃገራችን ያለው አመራር ፈር የለቀቀና ትውልድን የሚጎዳ እኔ ከሞትኩ ሠርዶ አይብቀል እንዳለቸው እንሰሳ ያለው አዝማሚያ እየታየ ነውና ሣይረፍድብን በአንድነት ቆመን ሃገራችንን ከጥፋት እናድን።

ስለዚህ እርስ በእርሱ ለመደጋገፍ መፍትሔ ለመሻት ወይም ግዴታቸውን ያልተወጡትን ለመሞገት አደባባይ ስንወጣ መሣሪያ በእኛ ወገናችሁ ላይ ከማሳታችሁ በፊት ሁለቴ አስቡ። ተኩሳችሁ ብትገድሉን የገደላችሁት እኛን አይደለም ራሳችሁንና ሃገራችሁን ነው። ከስንዴ ውስጥ እንክርዳድ አይታጣምና የጥፋት መልክተኞችን ጠቅቶ መጠበቁ አይከፋም።

የማን ሃገር ሠራዊት ነው የሃገሩን ሕዝብ ተኩሶ የሚገድለው? የሃገሩ ወሰን ሲደፈር፣ ለባዕድ ሲሸጥ መሣሪያውን አንግቦ ወደ ምግብ አዳራሽ የሚገባው? የማን ሃገር ሠራዊት ነው? አባት እናቱ እህት ወንድሙ ተርበው እያየ ዳቦ ሲሉ ተኩሶ የሚገለው? ድምፄ ይከበር በማለቱ መገደልስ ነበረበት? ክርስ መሬቴ ውስጥ ያለውን ሐብት አላስነካም በማለቱ የኦጋዴን ሕዝብ ቤት ንብረቱ ማቃጠል የገዛ እህቶቻችንን መድፈርስ አግባብ ነው? የሠራዊት አባላት ሰም ከአስጠፉ ጋር እንዴት ማዕድ ይቀረባል?

በሠራዊት ስም በአዲስ አበባ፣ በጋንቢላና በኦጋዴን የአጋዚ ብርጌድ የፈጸመውን ግፍ እንዴት ያየዋል። በሱማሊያ ተገድለው አስከሬናቸው በጎዳና የተጎተቱትስ ባልደረባዎቹ ደም ደመ ከልብ ሆኖ መቅረቱ አያሳዝንም? ወላጆች እስከአሁን እርማቸውን አላወጡም። ይህ ሠራዊት ነገ በኔን አያውቅም? ዘጎች አደባባይ ሰላማዊ ሠልፍ የሚወጡትእላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከሚመለከታቸው መልስ ለማግኘት ነው ። በምንከፍለው ግብር የሚያገለግሉን ሰለሆነ ዜጎች የሃገራቸው ጉዳይ የማወቅ ግዴታ አለባቸው። ተማሪው አስተማሪው ሠራተኛው ነጋዴው ገበሬው የሃገሬ ጉዳይ ያገባኛል በማለቱና ሰልፍ በመውጣቱ መደገፍና መበረታታት እንጅ በፌደራል ፖሊስና በአጋዚ ጦር መሣደድ የለበትም። ባይሆን እራስን ማግለል ይመረጣል።

ከትግራይ ሕዝብ ነፃነት ግንባር ጋር የሚሰሩ ሁሉ ማወቅ ያለባቸው የሕዝብ ጥያቄ የማንኛውም ዜጋ ጥያቄ ስለሆነ ከሕዝብ ጋር ብትቆሙ መልካም ፤ያ፡ ባይሆንላችሁ ግን ራሳችሁን ከመጥፎ ተግባር ብትታቀቡ ለሕዝብ ውለታ እንደሰራችሁ ይቆጠራል። በአንድ ወቅት አንበገርም ባዮች፤ አንባገነኖች፣በቃሬዛ ለፍርድ ሲቀርቡ፤ በሆስፒታል ለሞት ሲያጣጥሩ፤እንደ አይጥ በጉድጓድ ሲቅበዘበዙ እያየን ነው። ያም ሆኖ ተሸነፍን አይሉም። ተከታዮቻቸውን ለማዋለልና ብሎም ለማስጨርስ ከዚያም በመጨረሻው ሰዓት ባመቻቹት መንገድ ከነቤተሰባቸው ለመውጣት ጊዜ ለመግዛት ነው። ዛሬ በሰልጣን ላይ ሰላለው መለስ ዜናዊ ብልጣ ብልጥነት ትተውት ከወጡት የቅርብ ጓደኞቹ መረዳት ይቻላል። የሚያውቁትነና የሚቀርቡትን በአባሳደር ሰም ቦታ ቦታቸውን አሲዘሷቸዋል። አንዳንዶቹም ‘ፈረሰኛ ሲቀድም እግረኛ ምን ይጠብቃል’ በማለት ከሃገር ከወጡ አይመለሱም።

ከምርጫ 2003 ዓ ም ወዲህ ወደካቢኔ ጣጋ ያሉት እነ አልሰሚ ገቡ በላቸው ነውና መጨረሻውን አብረን የምናየው ይሆናል።

ለምሳሌ የሰሜን አፍሪካና የመካከለኛው ምስራቅ አንባገነኖች በሥልጣን ዘመናቸው የዘር ማጥፋት ወንጀል አልፈጸሙም ነበር። ክስም አልተመሰረተም።

ለፍርድ የሚቀርቡት አደባባይ በወጣው ሕዝብ ላይ ሠራዊቱ እንዲተኩስ ትዕዛዝ በመስጠታቸው ነው።
የኢትየጵያ መሪ ነኝ ባዩ መለስ ዜናዊ ግን በጋንቤላ፣ በኦጋዴንና በአዲስ አበባ በእርሱ ትዕዛዝ ለተፈጸመው ጭፍጨፋ ቀደም ሲል ሔግ ላይ ክስ ቀርቦበታል።
ጊዜ ይርዘም እንጂ ፍትሕ የማይቀር ነው። ካቦዲያ ውስጥ ከአርባ ዓመት በፊት አነ ፖሊፔን ለፈጸሙት ግድያ ለፍርድ ቀርበዋል።
የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍትሕ ይጠይቃል፣ ያገኘዋል።

ታደለ መኩሪያ
tadele@shaw.ca